ኢትዮጵያወያን ሜህበረሰብ በቤልጅግ

# Ethiopian community in Belgium (ECB)

ቀን፡ ህዳር 5, 2006 ዓም

**በሳውዲ ዓረቢያ በሚገኙ ኢትዮጵያውያን ላይ እየተፈጸመ ያለውን ኢሰባዊ ድርጊት የሚያወግዝ መግለጫ**

በአስገዳጅ ምክኒያቶች ከአገራቸው የተሰደዱ ኢትዮጵያውያን በልዩ ልዩ አገሮች የሚፈጸመባቸው እንግልትና ኢሰባዊ ድርጊት ከፍተኛ መሆኑ ቢታወቅም፣ ሰሞኑን በሳውዲ ዓረቢያ መንግስት እየየተፈጸመ ያለው ግን ፍጹም አረመኒያዊና ጭካኔ የተሞላበት በመሆኑ ሁሉም ሊያወግዘውና ሊፋረደው የሚገባ ነው።

በቤልጅየም የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ፣ የሳውዲ ዓረቢያ መንግስት፣ በአገሩ ሰርተው በሚኖሩ ትውልደ ኢትዮጵያውያን ላይ፣ ወታደር አስማርቶ፣ ቦዜኔዎቹን ለቆ፣ ማስደብደቡን፣ ማስደፈሩን፣ ማስገደሉንና ማዘረፉን አጥብቆ ያወግዛል። የሳውዲ መንግስት የሀይል እርምጃ ሰለባ ከሆኑት ኢትዮጵያውይን ጋርም ያለውን አንድነት እየገለጸ፣ ይህ ኋላቀር አረመኒያዊ የሳውዲ መንግስት ድርጊትም በዓለማቀፍ የሰባዊ መብት ተከራካሪ ድርጅቶች እንዲወገዝ ጥሪውን ያስተላልፋል።
በመስረቱ ኢትዮጵያውያን በገፍ እንዲሰደዱና ለእንደዚህ ዓይነት ችግር እንዲጋለጡ የተደረገው፣ በአገራቸው በነጻነት ሰርተው ለመኖር የሚያስችላቸው የፖለቲካና የኢኮኖሚ ሥርዓት ባለመኖሩ ምክኒያት ነው። ዜጎች ስደትን ምርጫቸው የሚያደርጉት አማራጭ ሲያጡ መሆኑ ግልጽ ነው። ኢትዮጵያ አገራችንም የህግ የበላይነት ያለባት፣ በነጻነት ሰርቶ የመኖር መብት የተረጋገጠባትና ህላፊነት የሚሰማው መንግስት የተመሰረተባት ብትሆን ኖሮ፣ እንዲህ ለግፈኞችና ወንጀለኞች የተጋለጡ የወጣት ስደተኞች ምንጭ ባልሆነች ነበር። ዜጎችን ከችግርና ከውርደት መታደግ የሚቻለው አገሪቱን የስደት መፈልፈያ ያደረጓትን የፖቲካና የኢኮኖሚ ስር ዓቶች በማሻሻልና በመቀየር ብቻ እንደሆነም ኮሚኒቲያችን ያምናል።

የኢትዮጵያ መንግስት በኢትዮጵያውያኑ ላይ እየተፈጸመ ያለውን ጥቃት፣ ግድያና ዘረፋ ለማስቆምና፣ ወደአገራቸው እንዲመለሱ ለማድረግ የሚያደርገው እንቅስቃሴ፣ ከዚህ ግባ የማይባል መሆኑን እራሳቸው ተጎጂዎቹ ከዚያው ከቦታው እየገለጹ ነው። ቀድሞውኑ በአገራቸው ስርተው መኖር የሚገባቸው ዜጎች ለስደት ተዳርገው እንዲህ በአደባባይ ሲዋረዱና ሲገደሉ ፈጥኖ ለመድረስ አለመቻል ደግሞ ትልቅ ወንጀል በመሆኑ በህላፊነት የሚያስጠይቅ ነው።

በመሆኑም በቤልጀየም የኢትዮጵያ ማህበር በሳውዲ በሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ላይ እየተፈጸመ ባለው ግፍና ስቃይ የተሰማውን ቁጭትና ሀዘን እየገለጸ፡

1. የሳዕዲ ዓረቢያ መንግስት ኢትዮጵያውያኑን ሰደተኞች በዓለማቀፍ የስደተኞች ህግ መሰረት እንዲያስተናግድና በኢትዮጵያውያኑ ላይ የሚፈጽመውን ግድያ፣ እስራትና ማዋከብ እንዲያቆም፣
2. ባለፈው አንድ ሳምንት በሳውድ ዓረቢያ በተለይም በሪያድ ከተማ በኢትዮጵያውያን ላይ የተፈጸመውን ግድያ፣ ዘረፋና አስገድዶ መድፈር የሚያጣራ ገለልተኛ ኮሚቴ እንዲቋቋምና ወንጀለኞቹ ለፍርድ እንዲቀርቡ እንዲደረግ ይጠይቃል።

የኢትዮጵያ መንግስት በቅድሚያ ዜጎችን ለስደት በመዳረጉ፣ እንዲሁም ለችግራቸው ፈጥኖ ባለመድረሱና ተገቢውን እርምጃ ባለመውሰዱ ተጠያቂ መሆኑን ኮሚኒቲው በአጽንኦት እየገለጸ፣ የኢትዮያውያን ስደት ሊገታና ስቃያቸው ሊያበቃ በሚችልባቸው የፖለቲካና የኢኮኖሚ ፕሮግራሞች ላይም፣ ሁሉም የኢትዮጵያ ሀይሎች በሃላፊነት ስሜት በጋራ እንዲሰሩ ዛሬም ጥሪውን ያቀርባል።

**የችግርና የስደት ምንጭ ይድረቅ!**
**የኢትዮጵያውያን ክብርና ሞገስ ይመለስ!**

በቤልጅየም የኢትዮጵያውያን ማህበር

በቤልጂዬም የኢትዮጵያ ማህበር በቤልጂዬም ህግ መሰረት በ 14/03/1996 ታትሞ በወጣው ሞኒቶር ጋዜጣ በምዝግባ ቁጥር 4934/96 የተመዘገበ ነው።

Ethiopian Community in Belgium
Helihavenlaan 55 Bus B2
1030 Brussel
e-mail: Ethiopian.community@gmail.com
URL : http://www.ethiobelgium.com
A/C : 734-0202765-44 , KBC